# ከእግዚአብሔር ፍቅር

“ ... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ::” (ኢሳ 48 ÷ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. /// አዘጋጅ መላኩ ማሞ ትዕዛዙ E-mail – hello@ethiogodslove.org

**ሰኔ** 1996 **June** 2004 “ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል::” (ኢሳ 54÷13)

አዘጋጅ :- መላኩ ማሞ ትዕዛዙ

# ዘጸአት

አምላክህ እግዚአብሔር ያከናውንልኛል ብለህ በምትጠባበቀው ነገር ተቃዋሚ ይበዛብሃል? የፀሎትህን መልስ እንዳትቀበል የሚያስፈራህ ምንድን ነው? አምላክህ ሊያወርስህ ቃል ወደ ገባልህ ሥፍራ እንዳትደርስ ዘመኑ ሲራዘምና ተቃውሞው ሲበረታ:- ከዕብራውያን ታሪክ÷ ከዘጸአት÷ ጠቃሚ ትምሕርት መውሰድ ይቻላል::

ዕብራውያን በግብፃውያን እጅ በባርነት ይማቅቁ ነበር:: አራት መቶ ዓመት በባርነት ውርደት ውስጥ ሆነው:- ወደ አምላካቸው የፀለዩት ፀሎት መልስ በመጣላቸው ጊዜ በሙሴ መሪነት የተደረገው ጉዞ ዘጸአት ይባላል:: ስለዚህ ዘጸአት፡ የነፃነት ÷ ተስፋን የመጨበጥ ÷ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመግባት የመነሣትና የመጓዝ ታሪክ ነው:: አምላካቸውን በማመን ድሉን በሚወርሱትና በማይወርሱት መሐከል ግልጽ ልዩነት የሚታይበት መጽሐፍ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱሳችን መግቢያ ላይ (ኦሪት ዘጸአት) ሁለተኛው መጽሐፍ ነው:: (አንብቡት)

## *ከዘጸአት የምንማረው:-*

*1. ከግብፅ÷ ከባርነት ወጥቶ በነፃነት ከነዓን ለመድረስ የፈጀው አርባ ዓመት ነበር::በእነዚህም ዓመታት ሕዝቡ ተፈትነው ታይተዋል:: በመሠረቱ መንገዱ ያንን ሁሉ ጊዜ መፍጀት አልነበረበትም:: ሆኖም ሕዝቡ ባለማመንና በማጉረምረም መንገዱን አራዘሙ:: አብዛኛውም ሕዝብ ከነዓን ሳይገባ በበረሐ አለቀ:: በዕምነት እግዚአብሔርን ተከትለው የተስፋዪቱን ምድር በመውረስ ፈንታ÷ከዮርዳኖስ ማዶ በቁጣው አለቁ:: እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ ያምኑና ይቀበሉ ዘንድ ሊታገሣቸው ሲል አጭሩን መንገድ ለአርባ ዓመት አራዘመላቸው:: ሆኖም ያ ትውልድ እስኪያልቅ ድረስ ደነደኑ እንጂ ወደ ዕምነት አልተመለሱም:: ድልና ስኪታቸው ወደ ሚቀጥለው ትውልድ ተላለፈ:: ከስለላ ተመልሰው የዕምነት ቃል የተናገሩትን ካሌብንና ኢያሱን እንኳ÷ ብዙዎቹ አላመኑአቸውም::*

*በዚህም ዘመን ÷ እግዚአብሔር የዕለት እንጀራን እንደሚሰጥ የሚያምኑና የሚፀልዩ ብዙ ሲሆኑ÷የተትረፈረፈ በረከት ግን÷እንኳንስ መቀበል መጸለይ እንኳ የሚፈሩ ብዙ ናቸው፡*

*አይሑድ በጠማቸው ጊዜ ከድንጋይ ውኃ አፍልቆ አጠጣቸው:: ምንም በሌለበት በበረሐ ከሰማይ መናን አውርዶ መገባቸው:: ይህ የዕለት መሻታቸው በተዓምር ሲሟላ አይተዋል:: ነገር ግን ከዚያ አልፎ ማርና ወተት ወደምታፈስ ምድር መግባት ዕምነታቸውን የሚፈትን ስለ ሆነ ደከሙ፤ ስለዚህ በጥቂቱ መርካት÷ በትንሹ መቅረት ዋጋቸው ሆነ:: ወገኔ:-እስከ ዚህ ያደረሰህ ጌታ እግዚአብሔር አምላክህ÷ ቸርነቱ የማያልቅበት መሆኑን አስተውል:: ኤቤንዔዘር ያልነውን መዝሙር ታስታውሳለህ?*

*እስከ ዛሬ ድረስ ረድቶናል፡*
*በድል በተዓምር መርቶናል፤*
*ወደ ፊትም ቢሆን ጌታ ያውቃል፡*
*ሁሉም በእርሱ ያልፋል::*

*ርግጥ ነው እስከ ዛሬ ድረስ ጌታ ያደረገልን ምሕረትና ቸርነት ያስደንቃል:: ጌታ ይህን ሁሉ የምታደርግልኝ እኔ ማን ነኝ ያሰኛል:: ይበልጥ የሚደንቀው ነገር ግን÷ ጌታ እንደ ያዕቆብ ለመባረክ የሚፍጨረጨሩ ልጆቹን ጨምሮ መባረክ መውደዱ ነው:: “የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና÷የሚፈልገውም ያገኛል ÷ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል” ያለው ለዚህ ነው:: (ማቴ 7÷8) ስለዚህ:-*

*ከማያልቅበት ጌታ÷ ከአምላክህ በረከትን ለመቀበል ወደ ፊት ከመዘርጋት አትቆጠብ:: ብዙ የተቀበልህ ቢሆንም÷ አምላክህ ከቶ አያልቅበትም:: ከድል ወደ ድል÷ ከበረከት ወደ ሌላ በረከት ቅጥሮችን መዝለል አይድከምህ::*

*2. “በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና” (ምሳሌ 23÷7) “ልጄ ሆይ÷አይዞሽ፡ ዕምነትሽ አድኖሻል” (ማቴ 9÷ 22) “..እንደ ዕምነታችሁ ይሁንላችሁ..” (ማቴ 9÷29) “...አንቺ ሴት÷ዕምነትሽ ታላቅ ነው እንደ ወደድሽ ይሁንልሽ...” (ማቴ 15÷28)*

*ሰዎች በልባቸው ያለጥርጥር የሚያምኑትና ተግተው የሚፈልጉት ነገር ይሆንላቸዋል:: ያለምንም ቀስቃሽ ተነሥተው ማድረግም ይችላሉ:: ሰዎችን ተከትሎ መሻገር ግን ብዙ ምክንያት ሊኖረው ይችላል:: የፈርዖን ሠራዊት ከኋላህ ሲኖር ÷ በዕምነት ተነሥተው ባሕሩ ውስጥ እግራቸውን የሚዘረጉ ደፋሮች ከፊትህ ሲኖሩ፡ ለመሻገር መቅረብ አያዳግት ይሆናል:: ጠላት ከኋላ÷ ደኅንነት ከፊት በግልጽ ሲታይ የሚደረግ ርምጃ ከፍርሃት ይሆን ከዕምነት አይታወቅም:: ነገር ግን “አሻግርሃለሁ” ያለውን የጌታ እግዚአብሔርን ቃል ብቻ ይዞ ውርስን ለመውሰድ መነሣት÷በዕውነት ዕምነት ይጠይቃል:: የኢያሱና የካሌብ ዕምነት:: እስራኤላውያን ግን በተስፋዪቱ ምድር ሊያጋጥሙአቸው ያሉትን ቁመተ ረዣዥም ተቃዋሚዎች በፈሩ ጊዜ የዚያን ትውልድ ዕጣ ክፍል ወሰኑ::*

*ዛሬም÷ ታላቅ መንፈሳዊና ቁሳዊ የበረከት ተስፋው እያላቸው÷ በሁኔታዎች ተበግረው የተቀመጡ ስንት የጌታ ልጆች ይኖሩ ይሆን?*

*ሰዎች የሚባረኩት ከአንተ ስለሚሻሉ ነው፡ የሚለውን የጠላት ውሸት ተቀብለዋል:: የተቀባ አገልጋይ÷ ጠቃሚ ምሑር ÷ ሐብታም ÷ ወይም ተወዳጅ የሐገር መሪ ለመሆን ልዩ ሰው መሆን አለብህ የሚላቸውን ሴይጣናዊ ሐሰት አምነው ከመፍጨርጨር ይገታሉ:: ዕውነቱ ግን እግዚአብሔር የከበረባቸውና ያስከበራቸው ኃያላንና ሐብታሞች ሁሉ እንዳንተው ያሉ ጉድለት ያለባቸው ሰዎች ናቸው:: መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ ታላቁ ነቢይ ሲናገር:- “ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ” ይላል (ይሁዳ 5÷17):: አንተ ብቻ ከጌታ ጋርና በፈቃዱ ውስጥ ሁን እንጂ ታላቅ ነገር በሕይወትህ ይሆናል:: ምክንያቱም፡ የቻሉትን ሁሉ ያስቻለው ጌታ አንተንም ስለሚያስችልህ ነው::*

*3. ተስፋቸውን ሳይቀበሉ በበረሐ የቀሩትን ዕብራውያን የፈጃቸው ቁመተ ረዣዥም ጠላታቸው አልነበረም፤ ፍርሐታቸው ነው:: ተስፋ የሰጠውን እግዚአብሔርን አለማመናቸው ነው ምንም እንኳ ሌላ አዲስ ትውልድ ተተሥቶ የተስፋዪቱን ምድር መውረሱ ባይቀርም÷በዚያ ትውልድ አለማመን የተነሣ፡ በሁለት ዓመት ያህል ጊዜ ውስጥ የእነርሱ መሆን የነበረበት ምድር ወደ አርባ ዓመት ተላለፈ፤ ጌታ ከዚህ ያድነን::*

*በአምላኩ የተማመነው ዳዊት ተነሥቶ ጎሊያድን ከጣለ በኋላ የፍልስጥኤምን ሠራዊት አሳድዶ ማሸነፍ ለቤተ እስራኤል ቀና ነበረ:: የአንተም ዕምነትና ድፍረት ለራስህ ብቻ ጥቅም ሳይሆን ለሚፈራው ጎረቤትህ የዕምነት ማስፈንጠሪያ ይሆናል:: ምክንያቱም ዕምነት ለዕምነት÷ስኬት ለሌላ ስኬት መነሻ ስለሚሆን ነው::*

*4. በሕይወትህ እንዲሳካልህ ማንም ሊያስገድድህ አይችልም:: አይሑድ ምንም እንኳ ብዙ ድንቅና ተዓምራት ያዩ ቢሆንም÷ተስፋቸው እንደሚደርስ ማመን አልቻሉም:: እንደ ኣለማመናቸውም ሆነባቸው:: ያ ትውልድ በረከቱ ቀረበት:: ጌታ ያለው ግን አልቀረም::በልባቸው የሞላው አለማመን÷በዓይናቸው ያዩትን ተዓምራትና በጆሮአቸው የሰሙትን የተስፋ ቃሉን አጨለመባቸው::*

*በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተመዘገቡት ታላላቅ ተዓምራት ሁሉ የበረቱቱን:- ፋሲካውን÷መቅሰፍቶቹን÷የቀይ ባሕርን መከፈል÷ በቀን በክብሩ ደመና መከለልንና በሌሊት በእሳቱ ዓምድ መመራትን በሕይወታቸው ቢለማመዱም÷እልፍ ብለው በዕምነት ርስታቸውን መጨበጥ አልቻሉም ይልቁንም የባርነትን ዘመን በትዝታ*

*ይናፍቁ ነበረ:: የለመዱት ውስንነት አስሮ በፊታቸው ከሚጠብቃቸው በረከትና ተስፋ አስቀራቸው:: ኢያሳዝንም?*

*<u>ስኬት ምን ጊዜም ቢሆን ባለፈው ላይ ለሚያተኩሩት ሳይሆን፥ ወደ ፊት ለሚዘረጉት የተሠጠች ናት::</u>*

*"ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፡ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፡መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል::"(ማቴ 7፥7)*

*ይህ የጌታ ምክር የሚያመለክተው፥ ወደ ፊት መዘርጋትን ነው:: ምክንያቱም ሰው ያለውን አይለምንም:: ያገኘውንም አይፈልግም:: የተከፈተለትንም በር አያንኳኳም:: እንዲከፈትለት የሚፈልገውን በር ግን ተግቶ ማንኳኳት ይጠበቅበታል::*

*5. ሰው፥ በማያምንበት ነገር ስኬት አያገኝም:: በዘጸአት ታሪክ ውስጥ እንደታየው:- የእግዚአብሔርን ቅር በትና ኃይል ከማንም ይልቅ የተለማመደው ትውልድ ነው ተስፋውን በ ዕምነት ለመቀበል የተቸገረው::መውጣትንስ ከባርነት ወጥተዋል:: ድነዋል:: ነገር ግን እንደ ታሰበላቸው ሳይ ባረኩ ሞቱ:: ከነፃነቱ እንጂ ከማሩና ከወተቱ ሳይቀምሱ አለቁ::*

*አዲሱ የእስራኤል ትውልድ የእሳቱንና የደመናውን ዓምድ ለራሱ አልተለማመደም:: <u>ነገር ግን ያልተበከለ ታዛዥና የዕምነት ሕዝብ ነው:: ስለ ሆነም ዮርዳኖስን ተሻግሮ፥ተስፋውን መጨበጥ:- ወደ እርሱ አለፈ::</u>*

*አብዛኛው ሰው ይሳካልኛል ብሎ ከማመን ይልቅ ኣለማመን ይቀለዋል::*

→

*የዚህ ክፋቱ ደግሞ ወደ ፊት የሚዘረጋበትን ራዕይና ዕምነት የሌለውን ሰው፥ እግዚአብሔር እንኳ ሊያነሣሣው የማያስገድድ መሆኑ ነው:: ማስገደድ ባሕሪዩ አይደለምና:: ስለዚህ <u>ጌታ በሰጠህ ተሰፋ ላይ በርታና ተነሣ:: ይሆንልህማል:: ተስፋ የሰጠህ አምላክህ እግዚአብሔር ተሳክቶልህ ለማየት ይጓጓል::</u> በዕምነት ታዝዘኸው ብትነሣ፥ በቀን የደመና ዓምድ:- በሌሊትም የእሳት ዓምድ ይደርስልሃል:: መነሣትህን ብቻ ነው የሚጠባበቀው:: <u>"መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል"</u> ጌታ ስሙ ይክበር::*

www.ethioGodslove.org

## ፍርድና ቁጣው

"እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል::"

(የሐ/ሥራ 17፥30-31)

"ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጉር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥በለስም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃሪያዋን ፍሬ እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፥ ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ:: የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም ባለጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባርያዎችም ጌቶችም ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ፥ተራራዎችንና ዓለቶችንም:- በላያችን ውደቁ በዙፋንም ከተቀመጠው ፊት፡ ከበጉም ቁጣ ሰውሩን፤ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም ይችላል? አሉአቸው::"

(የዮሐንስ ራዕይ 6፥12-17)

"ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ፤ ተራራዎችም አልተገኙም:: በሚዛንም አንድ ታላንት የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው..."(ዮሐ/ራዕይ 16፥20-21)

"በዚያን ወራት ግን ከዚያ መከራ በኋላ ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ:: በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ) በብዙ ኃይልና ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል::"

(የማርቆስ ወንጌል 13 ፥ 25-26)

*"እነሆ፥ከደመና ጋር ይመጣል፤ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል ፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ፡*

*(የዮሐንስ ራዕይ 1፥7)*

*"ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ::*

*(የዮሐንስ ራዕይ 20፥12)*

"ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል::" (ወደ ሮሜ ሰዎች 2፥16)

*"የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፡ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል::" (የዮሐንስ ወንጌል 12፥48)*

*"እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ፥ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን፥ወደ ፍርድ ያመጣዋልና፡"*

*(መጽሐፈ መክብብ 12፥14)*

"እንግዲያስ እያንዳዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን::"

(ወደ ሮሜ ሰዎች 14፥12)

*መልስ አለን? አጥጋቢ መልሳችንን ከአሁኑ ማዘጋጀት አይገባም? ? ? ? ?*

# በዚያን ጊዜ ከሚተላለፉ ሁለት ፍርዶች አንዱ:-

*"በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል:- እናንተ እርጉማን፥ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ::"*

*(የማቴዎስ ወንጌል 25፥41)*

*"በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ::" (የዮሐንስ ራዕይ 20፥15)*

*"...ትላቸው ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነም እሳት ከመጣል ... ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል::" (የማርቆስ ወንጌል 9 ፥ 46)*

*ወገኔ ሆይ:- በገሃነም ይግባኝ የለም:: ንሰሐም የለም:: መመለሻም የለም:: <u>ልባቸው እያወቀ</u>፥አእምሮን ጥለው፥ ስካር፥ ዝሙት፥ጥል፥ዘፋኝነት፥ምቀኝነት፥ስረቆት፥ መግደልን ወዘተ <u>የሚለማመዱ</u>:- የእግዚአብሔርን ስጦታ ኢየሱስንና ትምሕርቱን ችላ የሚሉ ሁሉ ወደዚያ ይጣላሉ:: <u>ነገር ግን ይህ የፍርድ ቀን ከመድረሱ በፊት የምሕረት ጌታ እግዚአብሔር የደኅንነትን መንገድ አዘጋጅቶአል:: እርሱም ልጁ የሆነው ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ነው::</u>*

*"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና"*

*(የዮሐንስ ወንጌል 3፥16)*

# *መድኃኒዓለም ይጠራሃል*

"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ::"

(የማቴዎስ ወንጌል 11፥28)



ከዘላለም ፍርድ ለመዳን የሚቻለው ኢየሱስንና ትምሕርቱን አምኖ በመቀበልና በመከተል ብቻ ነው::በኢየሱስ አምኖ ኃጢአትን መለማመድ ግን ከፍርድ አያድንም:: ስለዚህ ውሳኔ ለማድረግ ከልቡ የሚፈቅድ ሁሉ ንስሐ መግባት አለበት::መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና::

## <u>የንስሐ ፀሎት</u> :-

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ:: ስለኃጢአቴ የተሰቀለውን ኢየሱስንና ትምሕርቱን አምኜ እቀበላለሁ:: ስለዚህ ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፤ ወደ መንግሥትህ ተቀበለኝ:: በቀረኝ ዕድሜዬ አንተን ለማክበር እንድችል እርዳኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን:: **************

*ይህንን ፀሎት ከልብ በማመን ለመጀመሪያ ጊዜ የፀለያችሁ፥ በዚህ ደብዳቤ መግቢያ ላይ በተሰጡት አድራሻዎች ብታስታውቁን:- አስፈላጊ ምክሮችን ልንልክላችሁ እንችላለን:: በአካባቢያችሁ ወደሚትገኝ ወንጌልን ወደምትሰብክ ቤተ ክርስቲያን ልንጠቁማችሁ እንሞክራለን:: ወገኔ:-እግዚአብሔር ይወድሃል፡*

እንተርኔት አለዎት? ምርጥ መዝሙሮችን እያዳመጡ ደብዳቤዎቻችንን ማንበብ ሆነ አትሞ ለሌሎች ማካፈል ይቻላል።
www.ethioGodslove.org

*እየሱስ ጌታ ነው:: ጌታ ይባርክህ::*